እነዚህና ሌሎች በዚህ ውስጥ ያልተካተቱ ክንውኖች የገፏ ሽቀ ቀልተ እንዲፈስ ስያደረጉ፣ በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የግጭትና የመቆራቆስ ቁልታዎች እንዲበራከቱ አስገድ ዷል፡፡ በአራቱ ማዕዘን የሚያደርጉት የወያኔ–ሻዕቢያ የጸመነፍስ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችም የሰፈነው ውጥረት ዓይነተኛ ነፀብራቆች ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉም ሠላማዊ፣ ሕጋዊና ዲሞክራሲያዊ የትግል ማስወገጃ መንገዶችና መድረኮች ስለተነፈጋቸው መብታቸውንና ሕልውናቸውን ለማስከበር፣ ሀገራቸውን ከጥፋት ለማዳንና እነዚህን የሀገርና የሕዝብ ጠላቶች ለመደምሰስ የተለየ አማራጭ እንዲከተሉ ግዲታ ሆኗል፡፡

የአሁኑ ትውልድም ሆነ መላው ሕዝብ "ነግ በእኔ" በማለትና በአንዳንዱ የማለስለሻና የማዘናጊያ አቀራረቦች ባይታለል የእነዚህን የፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ቡችላ የሆነውን ዣጦራዊ ከህደት ጉዞ ከመኢሶንና ከሌሎች የነፃነት ተጋዳይ አርበኞችና ድርጅቶች ጋር በመተባበር ማፍረስ ታሪክ የጣለበት ወሣኝ ግዲታ ነው፡፡

ሀገራችንንና ሕዝባችንን ከጥፋት እናድን !
እናሸንፋለን !!